# ስጋትን ወደ ተስፋ የለወጠ ታላቅ መፅሃፍ....Tesfakiros Arefe

ስጋትን ወደ ተስፋ የለወጠ ታላቅ መፅሃፍ

መንደርደሪያ

I

1. ህወሓትን ለማወቅ ብዙውን የረዳን ተጋድሎ በሚል ኣምድ ስር በወይን ጋዜጣ ይስተናገድ በነበረ ፅሁፍ ነው፡፡ ይህ ፅሁፍ መሳጭና ያለምንም ጥያቄ እንዳለ የምንወስደው ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ኣምድ የህወሓት ክፍፍል ተከትሎ ይመስለኛል ጥራቱ ቀነሰ፣ከዛም ተቋረጠ፡፡ ከዚህ በኋላ የህወሓት አመራር ክፍፍል ተከትሎ ኣንድ ዳጎስ ያለ መፅሄት በህወሓት ይዘጋጃል፡፡ በዚህ መፅሄት ኣንዳንዶቹ ኣመራሮች ያልነበሩበትና ያልተወኑበት ታሪክና ገፀ ባህሪ ተሰጣቸው፣ በታሪኩ ተዋናይ የነበሩ ግለሶቦች ደግሞ ከትረካው እንዲወጡና እንዲገለሉ ተደረገ፡፡ ይህ መፅሄት በህዝብ ብቻ ሳይሆን በህወሓ ኣባላት ጭምር ሃዘንና ተስፋ መቁረጥን ኣስከተለ ፡፡ ከእንግዲህ የህወሓትና የትግራይ ህዝብ ታሪክ በትክክል ኣይፃፍም ወደሚል መደምደሚያም ኣመራ፡፡ ይባስ ብሎም Selfless የሆኑ ለህይወታቸው የማይሳሱ ጀግኖች አድርገን የምንቆጥራቸው እንደ ኣቶ ኣባይ ፀሃይ የመሳሰሉ የህወሓት ኣመራር ኣፈንጋጭ ተብለው የተፈረጁ ሰዎች ስም እንኳን ለመጥራት ያህል ሲፈሩ ስናይ ደግሞ ተስፋ መቁረጡ ወደ ላቀ ደረጃ ተሸጋገረ( ግማሹ የህወሓት መስራች ሃይል ወደ ህዝባዊ ግንባር ለስልጠና ሲሄድ ስየ ደክሞ ነበርና ኣባይ ኣዝሎ ተራራውን ያወጣዋል፡፡ ይህ ታሪክ በተራሮች ያንቀጠቀጠ ትውልድ ሰፍሯል፡፡ ይሽንን በተመለከተ ኣባይ ሲጠየቅ ጋዜጠኛው እስኪታዘበው ድረስ የስየን ስም ላለማንሳት ኣዎ ኣንድ ሰው ነበረ ብሎ በደፈናው ኣለፈው፡፡ በዚህ ኣባባሉ በኣባይ ያላዘነ ሰው ኣልነበረም፡፡ የኣባይም ስብእና ያመላከተም ነበር)፡፡

2. ኣንድ ወቅት ህያብ (ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ያለው) እና በርሃኑ ኣባዲ ኣንድ ካፌ/ሻይቤት ውስጥ ኣገኘኋቸውና ህያብ ‹‹በርሃኑ ይባላል ተዋወቀው፣ ስለ ኦፐሬሽን ኣግኣዚ መፅሃፍ ፅፏል ወደ ማተሚያ ቤት ሊገባ ነው›› ብሎ የመፅሃፉን ሽፋን ኣሳየኝ፡፡ እኔም ያው ችግር ኣለብኝና የሚሰማኝን ነገር ከመናገር ስለማልቆጠብ ‹‹የህወሓት ታሪክ እኮ ከእንግዲህ በትክክል ሊፃፍ ኣይችልም፣ የዚህ መፅሃፍ እድልም ተመሳሳይ ነው የሚሆነው›› ኣልኩኝ፡፡ ህያብ ቀበል ኣድርጎ ‹‹ብርሃኑ የኦፐሬሽን ኣግኣዚ ፈጣሪዋ/ኣፍላቂው ተወልደ ወልደማሪያም መሆኑን ታውቃለህ፣ ይሽንን ታሪክ ካለሰፈርከው ትክልል ኣይደለህም›› ኣለው( ተወልደ በኦፐሬሽን ኣግኣዚ የነበረው ሚና ስሰማ የመጀመሪያየም የመጨረሻየም ነው- ነገር ኣጥርቼ ካለወቅኩኝ እረፍት ስለማይሰጠኝ ሰሞኑን የብርሃኑ ኣባዲ ስልክ ኣፈላልጌ በአካል ኣግኝቼ ለመጠየቅ እያሰብኩ ነው፡፡ ኢንሻ ኣላህ)፡፡ ኦፐሬሽን ኣግኣዚ ግን ኣይደለም ብዙ ሰው የማያውቀውን የተወልደን ሚና ሊያሰፍር ሚናቸው በጉልህ የሚታወቅ ሰዎች እንኳን እንዲወጡ ተደርጓል ነው የሚባለው-መፅሃፉ ገዝቼ ካከማቸኋቸው ውስጥ ኣንዱነ ነው)፡ ቀጥሎ የስዩም መስፍን ታሪክ የሚያትት ፅንዓት መፅሃፍ ወጣ፡፡ የመፅሃፉን የተወሰኑ ገፆች ሳነብ ስዩም የተዛቡ ታሪኮችን እንኳን ከመፅሀፉ ይውጡ ለማለት ወኔ እንደሌለው ስረዳ ከእንግዲህ ስለ ህወሓት የሚፃፉ መፅሃፎች ኣንድ ወቅት እያመሳከርኩ ኣነባቸው ካልሆነ በስጠቀር በተናጠል ማንበቡ ወደ ስህተት መመራት ነው ብየ ወሰንኩና ስራየ እየገዛሁ ማስቀመጥ ሆነ፡፡ ኣሁን ከ 8-10 የሚሆኑ ህወሓትን የሚመለከቱ ያልተነበቡ መፃህፍት ኣሉኝ፡፡ ገላህቲ ሰጊ በሚል ርእስ ሙሉጌታ ደባልቀው የፃፋት ግን የተለየ ሁኔታ ስለነበራት ኣንብቢያታለሁ፡፡ ሙሉጌታ መፅሃፍ ላሳትም ነው ሲለኝ እኔም ወሬውን ለሌሎች ሰዎች ሳዳርስ ሰዎቹን ከኔ የተሻለ መረጃ ኖሯቸው ‹‹ኣዎ ኣዜብ እኮ በሜጋ በነፃ እያሳተመችለት ነው›› ኣሉኝ(መፅሃፉ ሲታተምም የትእምት ኩባያዎች በገፍ ገዝተውታል- የትእምት ስራ ኣስፈፃሚ ኣዜብ ናት )፡፡ በኋላ ሳጠያይቅ የኣቶ ስዩም ፅንዓት ለዚህ መፅሃፍ መነሻ እንደሆነች ሰማሁ፡፡ ኣዜብ ፅንዓትን ስታይ እንዴት መለስ ሳይፃፍለት የእነ ስዩም ታሪክ ይፃፋል ትልና ሙሉጌታ መፅሃፍ እንዲፅፍ ታደርጋለች፡፡ ታሪኩን ላሳጥረውና መፅሃፉን ካነበብኩ በኋላ ለሙሉጌታ እንዲህ ኣልኩት፡‹‹ ሙሉጌታ ለእንጀራህ ብለህ ብትፅፈውም እንደ ሌሎቹ ቀሽም ፀሃፊዎች ኣይደለህም፡፡ የስብእና ግንባታ/Cult Formation/Building ኣፃፃፍ ትችልበታለህ፡፡ የመለስን ስብእና በገነባህ ቁጥር ግን የሌሎቹን እየገዘገዝክ መሆኑን ሊገባህ ይገባል›› ኣልኩት፡፡ ተቃውሞ ኣላሰማኝም፣ ግንኙነታችንም ኣልሻከረም፡፡ ሙሉጌታ የህወሓት ከፍተኛ ካድሬ የነበረ፣ ከዚህ በተጨማሪም የመጀመሪያው ዲግሪው በፊሎዞፊ፣ ሁለተኛው ዲግሪ ደግሞ በሶሻል ኣንትሮፖሎጂ ስለሆነ የፖለቲካ ግንዛበው ጠለቅ ያለ ነው፡፡ የስዩም ፅንዓት ተፅእኖ በዚህ ላይ ኣላቆመም፡፡ ኣቦይ ስብሃትም የህወሓትን ታሪክ መርጠው ለማፃፍ ወደ ዩኒቨርሲቲና ብስራት ኣማረ ነው ያመሩት፡፡

II

1. እውነት ለመናገር የአቶ ገብሩ መፅሃፍ ለማንበብ ይኸን ያህል ጉጉት ኣልነበረኝም፡፡ ምክንያቴ ደግሞ በፅናታቸውና በቁርጠኝነታቸው እየተደነቅኩ የሁለት ኣመታት ግምገማ (ኣሁን ኣቶ ገብሩ ግምገማው ሶስት ኣመታት እንደፈጀ ይናገራሉ) ውጤታቸው በህዝባዊ ጋዜጣ ወጥቶ የኣፈንጋጮች ሃሳብ ለማንበብ በመቻሌ ነው፡፡ እና ኣጠቃላይ ሃሳባቸው በዚያ ዙሪያ የሚያጠነጥን መስሎኝ ብገዛውም ኣዲስ ነገር ስለማይኖረው ለማጠናቀቅ ብርታቱ ያጥረኝና እንደ ኣቶ ስየ መፅሃፍ ጀምሬ የምተወው ይመስለኝ ነበር፡፡ የህወሓት ሰዎች መፅሃፉን ሳያነቡ የኣቶ ገብሩን ስም ማጥፋት ሲጀምሩ ግን እንዲያ ሊያነጨረጭራቸው የቻለ ነገር ለማወቅ ከፍተኛ ጉግት ኣደረብኝ፡፡ እነዚህ ሰዎችና ደጋፊዎቻቸው ኣቶ በረከት የነገደ ጎበዜ መፅሃፍ እንዳስተዋወቁላቸውና ተነባቢ እንዳደረጉት ሁሉ የኣቶ ገብሩን መፅሃፍ በማስተዋወቅና ተነባቢ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

2. እውነትም ኣቶ ገብሩ የህወሓትን ፖለቲካዊ ታሪክ ከስረ መሰረቱ የሚያትት በድፍረት የተሞላና እና በመረጃ የታጨቀ መፅሃፍ ኣበርክተዋል፡፡ በሌላ በኩል ኣቶ ገብሩ ኣዲስ ኣጀንዳ ኣላቀረቡም ማለትም ይቻላል፡፡ የሳቸው መፅሃፍ ታሪካዊ ፋይዳው ከፍ የሚያደርገው ነገር በህዝብ ውስጥ ሲሽሎከሎኩ የነበሩ ጉዳዮች በመረጃ ኣስደግፈው ስላቀረቧቸው ተጨባጭ በማድረጋቸው ነው፡፡ የኣቶ ገብሩ ከፍተኛ ውለታም እዚህ ላይ ነው፡፡ የመጀመሪያውና ኣስቸጋሪው ምእራፍ እልባት ስለሰጡት ከኣሁን ወዲያ በእውነታ ላይ ጭቅጭ እንደማይኖር ተስፋ ኣደርጋለሁ፡፡ ቢኖርም መረጃዎቹን ከማጥራትና በመገለጫና ተጨማሪ መረጃ ከማቅረብ የዘለለ ሚና ኣይኖረውም፡፡ ውይይቱና የመረጃ ኣቀራረቡ ኣቶ ገብሩ ካስቀመጡት ማእቀፍ ስለማይወጣ ምእራፍ ኣንድ የተዘጋ ኣጁንዳ ኣድርገውታልና የሚቀረን ነገር ቆሞ ማሰብና ስለመቋጫው/መፍትሄው መነጋገር ነው፡፡

3. ኣቶ ገብሩ በህዝቡ ላይ የፈጠሩት ምስል ጠቅሚቸዋል፡፡ እነ ኣቶ መለስም ለዚህ ኣስተዋፅኦ ኣድርገዋል፡፡ በክፍፍሉ ጊዜ የእነ ኣቶ መለስ ቡድን ኣፈንጋጮቹን በሶስት ጎራ ከፍለዋቸው ነበር፡፡ ሙሰኛ፣ ኣምባገነንና ግትር በሚል፡፡ ኣቶ ገብሩ ድርቅና ካልሆነ በስተቀር ሃቀኛና መናጢ ደሃ ተደርገው ከየቀረቡት ውስጥ ናቸው፡፡ በየመድረኩ <<ገብሩ ለኣንድ ቀን እንኳን የሚበላው ነገር የለውም፡፡ ገብሩ ይዞ የወጣው ንብረት መነፀሩን ብቻ ነች>> እየተባለ በእነ ኣቶ መለስና ደጋፊዎቻቸው ይቀርብ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት የህወሓት ኣመራርን ኣስተሳሰብ በሚመለከት ያቀረቡልን መረጃ ያለምንም ማንገራገርና መጠራጠር እንዳለ ተቀብለናቸዋል፡፡ ስህተት ብናገኝ እንኳን ከዝንጋታ፣ ከመረጃ እጥረት ነው በለን እናልፈዋለን እንጂ እንደ ሌሎቹ ስብእናቸውን(Integrit ያቸውን) ኣልተጠራጠርናቸውም፡፡

4. ኣሁን የሚጠበቀው ነገር መፅሃፉን የተሟላ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ከተዋናዮች፣ ከኣንባቢና ከታሪክ ሰዎች በፅሃፉን በማደራጀት፣ በሞመረድ እና ቅርፅ በማስያዝ ብዙ ይጠበቃል፡፡

III

1. የማታ ተማሪ እያለሁ ጀብደኝነት ተሰማኝና ለኣስተማሪየ/ኣማካሪየ መመረቂያ ፅሁፌን በህወሓት የውስጥ ተግዳሮቶች/ችግሮችና ኣፈታታቸው ላይ ባደርገው ምን ይመስለዎታል? ስላቸው ተማሪዎቻችንን እንዲህ ኣይነት ሪስክ/ኣደጋ ውስጥ ኣናስገባም ኣሉኝና ተውኩት፡፡ ተዋናዮች በህይወት እያሉ ታሪካቸው ኣይፃፍም ይባል የለ፡፡ ተዋናዮች ተጠያቂነትን ፀሃፊዎች ደግሞ Consequence ስለሚሰጉ መረጃው በትክክል መውጣት ኣይችልም፡፡

2. ኣቶ ገብሩ እሳቸው ካልሆኑ የህወሓትን ታሪክ( በተለይ የልዩነት ኣየያዝና ኣፈታት በተመለከተ) ሌላ ሰው በዚህ መልኩ ሊፅፈው ኣይችልም፡፡ የሳቸው መረጃ ኣይደለም በታሪክ ፀሃፊዎች በተዋናዮቹ በራሳቸው እንኳን በዚህ መልኩ ሊቀርቡ ኣይችልም፡፡ መፅሃፉን የተሟላ ለማድረግ ደግሞ ራሱን ኣሳልፎ የሚሰጥ እንደ ኣውዓሎም የመሰለ ጀግና መኖር የግድ ይላል፡፡ የኢህኣፓ ታሪክ እስካሁን ኣጨቃጫቂ ሆኖ የቀረው ራሳቸውን ኣሳልፈው የሚሰጡ ገብሩና ኣውዓሎምን የመሳሰሉ ውስጥ ኣዋቂዎች ስለጠፉ ይመስለኛል፡፡

3. ለኔ በዚህ መፅሃፍ ራሱን ለታሪክ ፍርድ መስዋእት በማድረግ ጀግና ሆኖ የወጣው ኣውዓሎም ነው፡፡ መግለፅ ባልችልም ኣቶ ገብሩ ራሳቸው የኣውዓሎምን ያህል መስዋእት ኣላደረጉም የሚል ስሜት ኣለኝ፡፡ በዚህ መፅሃፍ ይበልጥ እንድናውቃቸው የተደረጉት ደግሞ ኣባይ ፀሃየ እና ስዩም መስፍን ናቸው፡፡ ለእነዚህ ሰዎች የነበረን ከፍተኛና ሚዛኑ ያልጠበቀ ግምት በዋነኛነት በ 1993 የህወሓት ክፍፍል እና በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት/ ፍፃሜ(ኣቶ ስዩምን በሚመለከት) የተሸረሸረ ቢሆንም የኣቶ ገብሩ መፅሃፍ ግን የበለጠ ኣጋልጧቸዋል፡፡ ኣቶ ገብሩ ኣቦይ ስብሃትና ኣቶ መለስ

ላይ ነው ብዙ ማስረጃ ያቀረቡት ትሉ ይሆናል፡፡ ነገር ግን፡ ኣንደኛ እነዚህ ሰዎች ጥሩም ይሁን መጥፎ ያራመዱት ሃሳብና የወሰዱት እርምጃ ከራሳቸው እምነት የፈለቀ እንጂ የሌላ ሰው ተፅእኖ እና ስጋት ኣድሮባቸው ኣይደለም (በኋላ ላይ ኣቶ መለስ ላይ የምእራባውያን ተፅእኖ ሊኖር ቢችልም)፡፡ ሁለተኛ. የቀረበው መረጃ ማጠናከሪያ እንጂ እነሱን በሚመለከት ከዚህ በላይ መደበኛም ኢ-መደበኛም በሆነ መልኩ ተንሸራሽሯል፡፡ ስለዚህ መለስና ኣቦይ ስብሓትን በሚመለከት ብዙም ኣዲስ ነገር ኣላየሁበትም፡፡

4. ሌላ በዚህ መፅሃፍ ጎልቶ የወጣው ህወሓት ነች፡፡ ህወሓት ከሌሎች ድርጅቶች የነበራት ግንኙነትና የበላይነት ጠብቃ የወጣችበት ሁኔታ የሌሎቹን ድርጅቶች የራሳቸው መረጃና እይታ ታክሎበት እውነታውን የተሟላ ማድረግ ቢቀርም ህወሓት እንደ ድርጅት ግን ህይወት እንዳለውና ጥሩም ይሁን መጥፎ፣ የስልጣን ውድድር ይሁን ሽር ቢኖርም ባይኖርም፣ የውይይቱ ጥራትና የተዋናዮቹ እውቀት የተደራጀ ይሁንም ኣይሁንም ህወሓት ግን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ምህዳር ውስጥ የተሻለ ክርክርና የሃሳብ ፍጭት የሚደረግበት ድርጅት ነው፣ ኣመራሩም ከፍተኛ ቁርጠኝነት ኣለው፡፡

IV

1. ኣቶ ገብሩ በመፅሃፋቸው ትግራይ ልዩ ተጠቃሚ ነበረች የሚለውን የእነ ኣቶ መለስና የመሃል ኣገር ፖለቲከኞች ኣመለካከት በኣምክንዮና በማስረጃ ኣስደግፈው መክተዋል፡፡

2. ኣቶ ገብሩ ኣይደለም የታገሉለትን ኣላማና የትግል ታሪካቸውን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገቡ እነ ኣቶ መለስን ሰሚ ባያገኙም ‹‹ህልውናችንን የሚገልፀውን የትግል ታሪካችን ለመደምሰስ›› ሞከሩ ብለው ይከሷቸዋል(ገ.347)፡፡ እና ኣቶ ገብሩ የታገሉነትን ኣላማ (Cause) እና የትግል ታሪካቸውን ጥያቄ ውስጥ ኣስገብተዋል የሚል ካለ በማስረጃ ኣስደግፎ ያቅርብ፡፡

3. ኣቶ ገብሩ ይቅርታ የጠየቁበት ጉዳይ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትለይ የኢትዮጵያን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ(በተለይ የወደብ ጉዳይ) ኣልሰራንም የሚል ነው፡፡ ኣሁንም እኔ እንደገባኝ ከህወሓት/ የሚለዩት በሁለት ነገር ብቻ ነው፡ ኣንደኛ. በወገንተኛ ዲሞክራሲ ኣስተሳሰብ፡፡ የሊበራል ዲሞክራሲ የሚመራበት መርህ Majority rule Minority Right ነው፡፡ ያሸነፉ ይመራሉ፡፡ የተሸነፉት ደግሞ መብታቸው ይጠበቅላቸዋል፡፡ በሶሻሊዝምና ወደ እርሱ መሸጋገሪያ የሆነው ኣብዮታዊ ዲሞክራሲ ግን ህዝብን በመደቦች ይከፋፈልና በኣጋር፣ በወዳጅና በጠላት ተፈርጀው ይቀመጣሉ፡፡ በዚህ ስርኣት ዲሞክራሲ ለወዳጅ እንጂ ለጠላት ኣይታሰብም፡፡ በዚህ መሰረት ኣሸናፊዎች ይመራሉ/ይገዛሉ፤ ተሸናፊዎች ደግሞ ይጨቆናሉ-ገፋ ሲልም ይጠፋሉ ወይም እንዲጠፉ ይደረጋል፡፡ ኣቶ ገብሩ ‹‹መለስ›› ብለው ሲያዩት ትክክል መስሎ ያልተሰማቸውና የተፋቱት ኣስተሳሰብ ኣንዱ ይኸ ነው፡፡ ሁለተኛው የባህር በርን በሚመለከት ነው፡፡ ኣቶ ገብሩ ከላይ እንደጠቀስኩት ኤርትራ ስትለይ ፍችው የኢትዮጵያን ጥቅም በማያስከብር መልኩ ነው የተከናወነው፣ ለወደፊቱም ከ 80 ሚሊዮን የሆነ ህዝብ ያላት ኣገር ያለ ባህር በር ልትኖር ኣይገባም፣ የፀጥታ ዋስትናችንም ስለሆነ ለወደፊቱም የባህር በር ያስፈልገናል የሚል ነው፡፡ እና በዚህ ጉዳይ ላይ ወደኋላ ሄደው ይቀርታ በመጠየቅ፣ ለወደፊቱም ያልተቋጨ ኣጀንዳ በማድረግ ከኢህኣዴግ ተለይተዋል፡፡ የባህር በር የሌለው መንግስት(ሃገር) ኣይፀናም የሚል ጠንካራ ኣቋም የነበራቸውና ከፍተኛ ኣርበኝነት የፈፀሙት በኣፄ ዮሃንስ ዋና ከተማና ቤተ መንግስት እየኖሩ ይኸንን ኣቋም ባያራምዱና በኣፄ ምኒልክ ዋና ከተማና ቤተ መንግስት ውስጥ ከሚኖረው ሃይል ባይለዩ ነበር የሚገርመው፡፡

V

1. ኣገርና ድርጅቱን ወደ ለውስብስብ ችግር የዳረጉት የህወሓት ችግሮች ሶስት ናቸው፡ በፊውዳል ቤተሰብ ውስጥ የነበረ ቁርሾ ወደ ፖለቲካዊ ኣቋምና ቂም በቀል መቀየሩ፣ የኤርትራ ጉዳይ የቀኝ ግዛት መሆኑና በነፃነት(በመለያየት) መፈታት እንዳለበት ኣቋም መያዙ እና ፀረ-ታላቅዋ ኢትዮጵያ ኣስተሳሰብ፡፡

2. ኣንደኛና ሁለተኛ ምንጫቸው ይገባኛል፡፡ ማገብት እንዴት የፀረ-ታላቅዋ ኢትዮጵያ ኣስተሳሰብ ሊያቀነቅን እንደቻለ ግን ሊገለፅልኝ ኣልቻለም፡፡ ግዛት በማስፋቱ የትግራይ መሳፍንት፣ ካህናትና ወታደሮች ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ኣሁን ያለችው ኢትዮጵያ ደግሞ ከሞላ ጎደል የተመሰረተችው በኣፄ ዮሃንስ ዘመነ መንግስት ነው፡፡ እንዲያውም ኣቶ ኣለማየሁ ኣበበ የኢትዮጵያ ህዝብ የኣንድነት መንፈስ ያጣጣመው ከግብፅ ጋር የተካሄደውና ኣፄ ዮሃንስ በድል የተወጡት ጦርነትና እና የጣሊያን መምጣት መካከል ባሉት 8 እና 9 ኣመታት ውስጥ ነው ይላሉ፡፡ ኣፄ ምኒልክ ከኣፄ ዮሃንስ

በኋላ በዘመነ ንግስናቸው ያካተቱት ኣካባቢ ቢኖር ምናልባት በምእራብ ኢትዮጵያ በቤንሻንጉልና በጋምቤላ ኣካባቢ ያለው ሊሆን ይችላል፡፡ ኤርትራን ደግሞ ለጣሊያን በመስጠት ኢትዮጵን ኣጉድለዋታል፡፡ ተስፋሚካኤል ትኩእም በኣፄ ምኒልክ ዘመንም ቢሆን ግዛት የማስፋቱ ሚና የትግራይ ሰው ለሚሏቸው እቴጌ ጣይቱ እና ራስ ጎቦና ነው የሚሰጡት፡፡ የትግራይ ህዝብም ራሱን ከማንም በላይ ኢትዮጵያዊ እና ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ተቆርቋሪ ኣድርጎ ነው የሚያስበው፡፡ እና ይህ የታላቋ ኢትዮጵያ ጥላቻ ከየት መጣ? ይኽንን ሃሳብ ያራምዱ ከነበሩ ውስጥ የማገብት መስራች ነገር ግን ህወሓት ኣንድም ጊዜ ስሙን ጠርታው የማታውቀው ዕቁባዝጊ የሚባል ሰው እንደነበረ ኣቶ ገብሩ በመፅሃፋቸው ጠቅሰዋል(ገ.33)፡፡ ስለዚህ ሰው ምንም የምናውቀው ነገር ኣልነበረም፡፡ ነባር ታጋዮች ሳይቀሩ ስለሱ ምንም ኣያውቁም፡፡ ኣቶ ገብሩም ዕቁባዝጊ በየነ በ 1969 በሕንፍሽፍስ ተጠርጥሮ እንደነበርና የኣክሱም ልጅ እንደሆነ የዘለለ መረጃ ኣልሰጡንም፡፡ የኔ ጥያቄ ይህ ግለሰብ ለምን እስከ ዛሬ በማገብት መስራችነት ስሙ ኣልጠቀሰም? በህይወት ኣለ ወይስ የለም? ማገብትን በመመስረት የነበረው ሚና ምንድን ነው? የሚገርመው ነገር ኣሁን ኢህኣዴግ ስቪል ሰርቫንቱን እና ካድሬዎቹን ለማሰልጠን በተዘጋጀው ሰነድ ኢህኣዴግ ኢትዮጵያ የምትባል ኣገር መፈጠሯን እንደሚቆጨው ተንፃበርቋል፡፡ የኣገር ምስረታና ግንባታ ሂደቱ ሳንካ ነበሩት ማለት ያባት ነው፡፡ ነገር ግን ኣገሪቷ ኣሁን ያለውን ቅርፅ በመያዟ መቆጨት ምን ይሉታል?

3. ሌላው የእነ ኣቶ መለስ የኣፄ ምኒልክ ኣድናቂነት እና የዲፕሎማሲ ኣካሄድና እርምጃ መገጣጠም የኣጋጣሚ ጉዳይ ወይስ የኣፄ ምኒልክ ተፅእኖ ኣድሮባቸዋል፡፡ የእነ ኣቶ መለስ በባህር በር/ወደብ ጉዳይ ያላቸውና የነበራቸው ኣስተሳሰብ፣ ከውጭ ሃይሎች ጋር የሚደረጉ የልምምጥ ግንኙነቶች(ጣሊያንና ህዝባዊ ግንባር/ህግደፍን፣ ሌሎች የኣውሮፓ ኣገሮች እና ኣሁን የምእራባውያን ሁኔታን እንደ ኣብነት መውሰድና ማነፃፀር ይቻላል)፣ ሃገራዊ ጥቅሞችና ኣሳልፎ በመስጠት ወዘተ፣ ተመሳሳይነታቸው ሲታይ ይደንቃል፡፡ እና ይህ ግጥጥሞሽ የኣጋጣሚ ጉዳይ ወይስ የመወራረስ?

VI

1. ኣቶ ገብሩ የታሪክ ኣማካሪ ያስፈልጋቸው ነበር፡፡ ከኣክሱም እስከ ኣፄ ምኒልክ ያለውን ዘመን ሲዳስሱ የታሪክ ግድፈቶች ፈፅመዋል፡፡ የሚገርመው ደግሞ ኣፍንጫቸው ስር ያለው የቀዳማይ ወያነ ታሪክ እንኳን በትክክል ማስፈር ኣለመቻላቸው ነው፡፡ ከኣቶ ገብሩ መፅሃፍ የኢትዮጵያ ታሪክ ለፖለቲከኞች ምን ያህል ኣስቸጋሪ እንደሆነ ነው የተረዳሁት፡፡ እዚሁ በፌስ ቡክ ያለው ንትርክም ከፖለቲካ ፍላጎትና ጥቅም በተጨማሪ የግንዛቤ ችግር የፈጠራቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ችያለሁ፡፡

2. ህግዴፍ በኦፊሻል ስሙ ሻዕብያ ተብሎ እንደሚጠራ እርግጠኛ ኣይደለሁም፡፡ ይህ ካልሆነ ግን መፅሃፉ ታሪካዊ ሰነድ ነውና ነጥብ ከማስቆጠርና ከስሜት ተወጥቶ በኦፊሻል ስሙ ቢጠራ ይበጃል የሚል እምነት ኣለኝ፡፡

3. ኣቶ ገብሩ ኦዴንሳቸው የኣማርኛ ተናጋሪ ኣደረጉና በትግራይ ያሉ የሰውና የቦታ ስሞችን ረን በሬ(ሽረ-ሽሬ)፣ ሰን በሴ(ሽረ-እንዳስላሰ፡ ሽሬ እንዳስላሴ)፣ ሀን በሄ(በርሀ-በርሄ)፣ ኣን በአ እና ዓ(ኣውዓሎም-ዓውአሎም)፣ ነን በኔ(ወያነ-ወያኔ)፣ቐን በቀ እና ለን በሌ(መቐለ) ወዘተ እየተኩ ፃፉት፡፡ ይህ ፊደሉን በማያወቅት ታይፒስቶች የተፈጠረ ስህተትና ከለቀማ ያመለጠ ሊሆንም ይችላል፡፡ ስሞች ግን በተቻለ መጠን ቢጠበቁ ይሻላል፡፡ የቋንቋው ተናጋሪ ያልሆነ ሰው ከቅላፄ ችግር ቢሳሳት ምንም ኣየይደለም፡፡ የቋንቋው ተናጋሪ ግን ለመቀየር ምንም ምክንያት የለውም፡፡

4. Smooth, House Hold Item የሚሉ የእንግሊዘኛ ቃላት እርግጠኛ ባልሆንም እንደ ቅደም ተከተላቸው የተመቻቸ(ኣልጋ ባልጋ) እና የተለመደ(የተዘወተረ) የሚል ትርጉም ሰጥተውኛል፡፡

VII

1. ዘርኣይ ሃለማርያም የተባለ የፌስ ቡክ ማህበረሰብ ኣባል የኣቶ ገብሩ መፅሃፍ ህወሓት/ኢህኣዴግ፣ ትምክህተኞች እና የኤርትራ መንግስት (ህግዴፍ) ከጠሉት ማን ሊወደው ነው? ብሎ ሲጠይቅ ምናልባት የትግራይ ህዝብ የሚል መለስ ወርውሬለት ነበር(እሱም በእኔ ኣባባል ተስማምቷል)፡፡ ኣሁን መፅሃፉን ሳነበው ግን በእርግጠኝነት ይህ መፅሃፍ የትግራይ ህዝብ ቅርስ ነው፡፡ ታሪኩ ልጆቹ ፖለቲካዊ ኣስተሳሰባቸውን እንዴት እንደቀረፁ፣ ልዩነታቸውን እንዴት ይፈቱ እንደነበር፣ ከውጭና ከውስጥ ፖለቲካዊ ሃይሎች የነበራቸው ግንኙነትና ውጤቱን ወዘተ የሚመለከት የተዘገበበት ሰነድ ነው፡፡ ከዚህ ታሪክ የምንማርበትና የምንወስደውን የመለየት ደግሞ የቀጣዩ ትውልድ የቤት ስራ ይሆናል፡፡ ከዚህ

በተጨማሪ በመፅሃፉ የተነሱ ኣገራዊና ክልላዊ ጉዳዮች ከትግራይ ህዝብ ጥቅምና እይታ ኣንፃር ሃገራዊና ክልላዊ ጉፌዳዮች እንዴት ተቀርፀው እንደነበርና ለወደፊቱስ እንዴት መቀረፅ እንዳለባቸው የሚያወሱ ናቸው፡፡ ይህ ተጋሩ የክልልና የኣገር ጉዳይ እንዴት ያራምዱት እንደነበርና ለወደፊቱ እንዴት ማራመድ እንዳለበናቸው፣ ከዚህ በተጨማሪም በኣገር ደረጃ ሊፈጥሯቸው ስለሚገቡ ግንባሮችና ፖለቲካዊ ውህደቶች፣ ከኣሁን በፊት ጭምር ግንባርና ውህደት ለመፍጠር ያደረጓቸው ጥረቶችና ውጤታቸውን የሚያትት ነው፡፡ ኣቶ ገብሩ ኣስበውበት ይሁን ኣይሁን ሌላ ጉዳይ ሆኖ መፅሃፉ ላይ የተስተናገደው ኣስተሳሰብ የትግራይ ፐርስፔክቲቭ/ኣተያይ ነው፡፡ በባህር በር ላይ ያላቸው የልዩነት ምንጭም ወደ ትግራይ ህዝብ፣ መሳፍንትና ነገስታት የኣርበኝነት ተጋድሎና ህልም የመመለስ ኣዝማሚያና ጥረት ተደርጎ ሊወሰድም ይችላል፡፡

2. ይህ ኣጠቃላይ እይታየ ሲሆን ዝርዝር የሆኑ ጉዳዮች ግን እመለስባቸዋለሁ፡፡ የትኩረት ኣቅጣጫየም መፅሃፉን ለማዳበር ይጠቅሙ የምላቸው ሃሳቦች ከመጠቆም የዘለለ ኣይሆንም፡፡ በዚህ መሰረት የተሳሳቱ መስለው የተሰሙኝን፣ ግልፅ ያልሆልኝና የእይታ ልዩነት መስሎ የተሰሙኝን ለመጠቆም እሞክራለሁ፡፡

ቸር እንሰንብት